# የጨረታ ማስታወቂያ

## D.M.U./N.C.B.24/2015

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በ2015 በጀት ዓመት ከመንግስት በተፈቀደለት በጀት ለዋናው ግቢ Student's Cafe (G+0 Building) በደረጃ GC Grade 5 Or BC Grade 4 and Above/ እና በላይ ባላቸው ተቋራጮች በግልፅ ጫራታ አወዳድሮ ማሰራት ይፈልጋል፡፡ ስለሆነም በጨረታው የሚሳተፉ ተጫራቾች ከዚህ በታች ማለትም፤

1. በዘመኑ የታደሰ የንግድ ስራ ፈቃድ እና የቲን ምዝገባ ያላቸው፤የግብር ከፋይነት የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆኑ የተመዝጋቢነት ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፤
2. ለግንባታ ስራ የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል፣ማቴሪያልና ማሽነሪዎችን ሙሉ በሙሉ በራሱ አቅርቦ መስራት የሚችሉ ፣ በደረጃ GC Grade 5 Or BC Grade 4 and Above/ እና በላይ ያላቸው እና የጨረታ ማስከበሪያ የሚሆን ብር 460,000.00(አራት መቶ ስድሣ ሽህ ብር) በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ ወይንም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ስም አሰርቶ ማቅረብ የሚችሉ፡፡
3. ከላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ የስራ ተቋራጭ የጨረታ ሰነዱን የጫራታ ማስታወቂያው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በተከታታይ 21 ቀናት በስራ ሰዓት ከደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ አስተዳደር ህንፃ ቁጥር 27 ቢሮ ቁጥር 10 ወይንም አዲስ አበባ 4 ኪሎ ከቅድስት ማሪያም ቤ/ክርስቲያን ወረድ ብሎ ዋሚና ካፌ ላይ 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 7 ከሚገኘው ቢሮአችን የማይመለስ ብር 200.00/ ሁለት መቶ ብር/ በመክፈል የጫራታ ሰነዱን መግዛት ይችላሉ፡፡
4. የጨረታውን ፋይናንሻል ኦርጅናል እና ኮፒ ፣ ቴክኒካል ኦርጅናል እና ኮፒ ፣የጫራታ ማስከበሪያ እንዲሁም አስፈላጊ ሰነዶችን ለየብቻ አስተማማኝ በሆነ ማጣበቂያ በታሸገ ፖስታ በማድረግና በእያንዳንዱ ፖስታ ላይ የአሰሪ መ/ቤቱንና የተቋራጩን ሙሉ ስምና አድራሻ በመፃፍ ማህተም በማድረግ በተጠቃለለ አንድ ፖስታ በማሸግ ማቅረብ አለበት፡፡
5. ተወዳዳሪዎች የጨረታ ሰነዱን በአግባቡ በመሙላትና በማሸግ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ህንፃ ቁጥር 27 ቢሮ ቁጥር 10 ድረስ በመቅረብ ጋዜጣው ከወጣበት ቀን ጀምሮ ከተከታታይ 21 ቀናት በኋላ በ22 ኛው ቀን ከጠዋቱ 3:59 ድረስ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ሲኖርባቸው ጨረታው በዚሁ እለት ከጠዋቱ 4:00 ሰዓት ላይ ተዘግቶ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት 4:30 ላይ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ህንፃ ቁጥር 27 ቢሮ ቁጥር 10 ውስጥ ይከፈታል፡፡ሆኖም ተጫራቾች በጨረታው ላይ መገኘት ካልቻሉ መስፈርቱን እስካሟሉ ድረስ በጨረታው ላይ ያልተገኙ ተጫራቾች ፖስታ ጨምሮ በእለቱ ይከፈታል፡፡
6. አሸናፊው ድርጅት አሸናፊነቱ በተገለፀለት ከ7ተከታታይ የስራ ቀናት በኋላ በግንባር ቀርቦ አሸናፊ የሆነበትን ጠቅላላ ዋጋ 10% የውል ማስከበሪያ በማስያዝ በ8 ቀናት ውስጥ ውል መያዝ ይኖርበታል፡፡

የበለጠ መረጃ ለማግኘት በስልክ ቁጥር 058 771 66 91/058/178 00 37/ ደውለው መጠየቅ ይችላሉ፡፡

- የጨረታ መክፈቻ ቀኑ የበአል ቀናት ወይም ቅዳሜና እሁድ ከሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን የሚከፈት ይሆናል፡፡
- ዩኒቨርሲቲው ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ደብረ ማርቆስ ኒቨርሲቲ**

Debre Markos University Procurement Administration Process